| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | መሥራች ፡ ጽሑፍ ። |
| ርእስ ፤ | "የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፦ ሥልጡንሕዝብና ።<br>የሥልጡንሕዝብና ፡ አመጣጥ ፡ በሀገረ ፡ ኵሽ ። " |
| ደራሲ ፤ | ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ። |
| ዕለት ፤ | ታኅሣሥ ፡ 1985 ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ 2011.002 ። |
| ማስታወሻ ፤ | ከ 26 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥ በድጋሚ ፡ የወጣ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

## መሥራች ፡ ጽሑፍ ።

founding article | article fondateur

# የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፦ ሥልጡንሕዝብና ።

## የሥልጡንሕዝብና ፡ አመጣጥ ፡ በሀገረ ፡ ኵሽ ።

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

(ሥልጡንሕዝብና ፥ 3ኛ ፡ ዓመት ፥ ቍ.006 ፥ ነሐሴ ፡ 1985 ፡ ዓ.ም. ። )

እንዳገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪክ ፥ በተለይም ፡ ከምሁራን ፡ ማኅበር ፣ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ አደባባይና ፡ ከጨዋ ፡ ሸንጎ ፡ እንደሚሰማው ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፥ ጥንት ፥ በመሠረት ፥ ኻያ ፡ ስምንቱ ፡ አንጋደ ፡ ኵሽ ፥ አባታቸው ፡ እንደ ፡ ሞተ ፥ በሥልጣኑ ፡ ሊተካ ፡ የሚገባው ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ ያስተዳዳሪነት ፡ ተሰጥዎ ፡ የለውም ፡ ብለው ፥ አለው ፡ ያሉትን ፡ ሰባተኛውን ፡ ልጅ ፥ አቢስን ፡ መርጠው ፡ ሊሾሙ ፡ ሲነሡ ፥ በሥልጣኑ ፡ ሥያሜ ፡ ተጣሉ ። የሚያስማማቸውን ፡ አገባብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲጠበቡ ፡ — ፡ "ፈልጉ ፡ ታገኛላችኹ" ፡ ነው ፡ — ፡ አመቺ ፡ ኹኔታ ፡ አጋጠማቸው ።

ፈጣሪ ፡ የውሃ ፡ ጥፋትን ፡ እንዳነሣ ፥ ከኖኅና ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ የገባውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፥ ካም ፥ በብሔረ ፡ አዜብ ፡ በኖረበት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፥ በበኩሉ ፡ ለማደስ ፥ በያመቱ ፡ መፈጸሚያ ፡ ሰሞን ፥ እወንዝ ፡ እየወረደ ፡ ሲጠመቅ ፥ ምልክቱ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ በየቀኑ ፡ ጧት ፡ በፀሐይዋ ፡ ጨረር ፡ ከውሃው ፡ ሲነሣ ፥ ያምላኩን ፡ ቸርነት ፡ በይባቤ ፡ እያወደሰ ፥ አምልኮቱን ፡ በሰጊድ ፡ እያደሰ ፡ ቈይቶ ፥ የመዝክረ ፡ ዓምን ፡ (የመስከረምን) ፡ መባቻ ፡ በወግ ፡ በማክበር ፥ ዐላፊውን ፡ ዘመን ፡ ሸኝቶ ፥ መጪውን ፡ ይቀበል ፡ ነበር ። ልጆቹም ፡ አንጋደ ፡ ኵሽ ፥ ይህኑ ፡ አምልኳዊ ፡ ደንኛ ፡ ልማድ ፡ አልተዉም ፡ ነበርና ፥ በዚሁ ፡ ወቅት ፣ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ እወንዝ ፡ ከትተው ፡ ተሰብስበው ፡ አሉበት ፡ ያስማሟቸው ፡ ዘንድ ፥ ብሶታቸውን ፡ ለነገድ ፡ አባቶቻቸው ፡ አመለከቱ ።

እነርሱም ፡ መክረው ፣ ዘክረው ፥ "አኹን ፡ እንዳደረጋችኹት ፡ ኹሉ ፥ ለወደፊቱም ፡ አሳዳሪያችኹን ፡ እናንተው ፡ በስምምነት ፥ ሲያስፈልግም ፡ በዕጣ ፡ ምረጡ ። ቀጥሎም ፥ ሊታመኗችኹ ፡ ባሕርያቸው ፡ የሚያስገድዳቸው ፥ ሊያውቁላችኹም ፡ ግንዛቦታቸው ፡ የሚፈቅድላቸው ፡ የነገድ ፡ አባቶቻችኹ ፡ መክረው ፣ ዘክረው ፡ የሚወስኑትን ፡ ሕግ ፡ አድርጎ ፥ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ ሳያበላልጥ ፥ በእኩል ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ እንዲያሳድራችኹ ፡ ተዋደዱ ፤ ከዚያም ፥ ውዴታችኹን ፡ የኹሉ ፡ ግዴታ ፡ አድርጎ ፡ እንዲያሳድራችኹ ፡ ጠይቁት ። ሲቀበል ፥ ማስፈጸሚያውን ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሠይሙት" ፡ ብለው ፡ መከሯቸው ። ምክራቸውን ፡ ወደው ፡ ተቀበሉ ፥ ፈቅደውም ፡ ታረቁ ። ወዲያውም ፥ በኹላቸውም ፡ ስምምነት ፥ አቢስን ፡ ጠርተው ፥ ውዳቸውን ፡ አፍስሰው ፥ "ታዲያስ ፥ ዐደራውን ፡ ልትቀበለን ፡ ትፈቅዳለኽን ፦ " ፡ ብለው ፡ ሲጠይቁት ፥ ፈቃዱ ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጦላቸው ፥ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ በወግ ፡ አሰሩ ። በርሷም ፡ ጸጋ ፥ በእኩል ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ወሰን ፥ በኹለት ፡ ፊት ፡ እታፈፈ ፥ በኹለት ፡ ፊት ፡ እኩል ፡ ተመዛዛኝነት ፡ እረጋ ፡ ዛኅን ፡ ላይ ፡ ያረፈውን ፡ ርትዐት ፡ ወይም ፡ የርትዕ ፡ ችሎት ፡ አሰፈኑ ። በርሱም ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ አዘዙ ፤ ሠለጠኑ ። ኻያ ፡ ስምንት ፡ አንጋደ ፡ ኵሽ ፡ የነበሩትን ፥ በፈቃዳቸው ፡ ተዋሕደው ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ አቢስን ፡ ኾኑ ። አቢስ ፣ አቢሴ ፣ አቢሳን ፡ ተባሉ ። ባንድነታቸውም ፡ የወል ፡ እግዚእናቸውን ፡ ተቀዳጅተው ፥ ሀገራቸውን ፥ ሀገረ ፡ ኵሽን ፡ በስማቸው ፡ አቢስያ ፣ አበሳንያ ፣ ሀገረ ፡ አቢስ ፡ አሠኙ ። የሚተዳደሩበትን ፡ ሕግ ፡ የሚመክርላቸውን ፡ ሀገራዊ ፡ የዐናት ፡ ሕዋስ ፥ በነገድ ፡ አባቶቻቸው ፡ ኅብረት ፡ "አባት" [1] ፡ ሠርተው ፥ ቀዳሚውን ፡ የርትዕ ፡ ዐልጋቸውን ፡ ዘረጉ ። ምርጣቸውን ፡ አቢስን ፡ ጠርተው ፥ "ሐፃኒ" ፡ ብለው ፡ አነገሡት ። በርሱም ፡ የመዠመሪያውን ፡ ሥልጡን ፡ መንግሥታቸውን ፡ አቆሙ ፤ ሠለጠኑ ። ለእግዚእናቸው ፥ በእግዚእናቸው ፡ ለሠሩት ፡ መንግሥት ፥ እኩል ፡ ዜጋው ፥ ታማኝ ፡ ሎሌው ፡ ኾነው ፡ ተገዙለት ፤ ሠለጠኑ ።

እንሆ ፥ እዚህ ፡ ድርስ ፡ ላይ ፥ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ በስምነቱ ፡ ተለይቶ ፡ አይጠራ ፡ እንጂ ፥ አቢሳን ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ሲያዙ ፥ ራሳቸው ፡ ለራሳቸው ፡ ሲታዘዙና ፥ አንዳቸው ፡ ለኹላቸው ፥ ኹላቸው ፡ ላንዳቸው ፡ ሲውሉ ፡ በሠለጠኑት ፡ እነርሱ ፥ ባካሉ ፡ ገዝፏል ፤ በግብር ፡ ውሏል ። ግብርም ፡ ለስም ፡ ያበቃል ፤ እንዲጠሩበትም ፡ ያስገድዳል ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ ግብሩ ፡ አጕልቶ ፡ ቀርጾ ፥ ለይቶ ፡ ባሳወቀው ፡ ስሙ ፥ ባለቤቱን ፡ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ ብለን ፡ ልንጠራው ፡ ይገባናል ።

ፍጡር ፡ የተፈጠረለትን ፡ ተግባር ፡ ማከናወን ፡ ባሕርያዊ ፡ ግዴታው ፡ ነው ። አቢሳን ፥ ጧት ፡ ሊለያያቸው ፡ የመጣባቸውን ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ያስወግድላቸው ፡ ዘንድ ፥ የፈጠሩት ፡ አንድ ፡ ሕዝብናቸው ፥ ባንድነታቸው ፣ ላንድነታቸው ፡ እየሠራ ፥ ከቶ ፡ ማን ፣ ምን ፣ የት ፡ ተገኝቶ ፡ ይለያያቸው ፦ ምስጋን ፡ ለሥልጡን ፡ አንድነታቸው ፡ (ለሥልጡንሕዝብናቸው) ፥ እንደ ፡ ተመኙት ፡ ኹሉ ፥ አደጋውን ፡ አስወግዶ ፡ ከጥፋት ፡ አዳናቸው ።

(ይቀጥላል ። )

1 አባት ፤ ("ባ" ፡ ይላላል) ፡ [አዘጋጅ] ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።